#DEFYHATENOW

# ማህበራዊ ሚዲያ እና የጥላቻ ንግግር

# የጥላቻ ንግግር መመሪያ

## ፌስቡክ

የጥላቻ ንግግር የሚከተሉትን መሰረት በማድረግ ሰዎች ላይ ቀጥተኛ ጥቃት ማድረስን ያካትታል፡ ዘርን፣ ብሄርን፣ የመጡበት ሃገርን፣ ሃይማኖትን፣ ፆታዊ ዝንባሌን፣ ፆታን ወይም የፆታ ማንነትን ወይም ከፍተኛ የሆነ የአካል ጉዳትን ወይም ህመምን።

## ኢሞ

የጥላቻ ንግግር: ኢሞ፥ ብዝሃነትን ያቅፋል እናም እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል ከተለያዩ አካባቢዎች ከመጡ ሰዎች ጋር እንዲገናኝ እና እንዲወያይ እናበረታታለን፡፡ እባክዎን በዘር፣ በጎሳ፣ በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በፆታ ማንነት፣ በጾታ ዝንባሌ፣ በሃይማኖት፣ በአካል ጉዳተኝነት ወይም በበሽታዎች ላይ በመመርኮዝ በማንም ላይ ጥቃት አያድርሱ፡፡

## ቴሌግራም

በቴሌግራም ቻናሎች ላይ ጥቃትን የሚያበረታታ ነገር ላለማስተዋወቅ ተስማምተዋል፡፡

## ትዊተር

የጥላቻ ድርጊት፡ ዘርን፣ ብሄርን፣ የመጡበት ሃገርን፣ ፆታዊ ዝንባሌን፣ የፆታ ማንነትን፣ ሃይማኖታን፣ እድሜን፣ የአካል ጉዳትን ወይም ህመምን መሰረት በማድረግ በሌሎች ሰዎች ላይ ቀጥተኛ ጥቃት እንዲደርስ ማበረታታት ወይም ማስፈራራት አይችሉም። የጥቃት ዛቻ (ቀጥተኛም ይሁን ተዘዋዋሪ) ማድረግ አይችሉም።

## ዋትስአፕ

የእኛን አገልግሎት ለህገወጥ እና አፀያፊ ድርጊቶች፣ መልካም ስምን ለማጉደፍ፣ ለዛቻ፣ ለማስፈራራት፣ ለማንቋሸሽ፣ ለጥላቻ፣ ለዘረኝነት ወይም አንድን ብሄር ለማንቋሸሽ ወይም ህገወጥ ሊሆን የሚችልን ነገር ወይም አግባብ ያልሆነ ድርጊትን ለማስጀመር ወይም ለማበረታታት፣ የጥቃት ወንጀሎችን ለማበረታታት፣ ሃሰተኛ መረጃዎችን ለማሰራጨት፣ ሃሰተኛ ውክልናዎችን ወይም ሃሰተኛ መግለጫዎችን ለማድረግ መጠቀም አይችሉም።

## ዩቲዩብ

ዩቲዩብ ላይ የጥላቻ ንግግር አይፈቀድም። የጥላቻ ንግግር በግለሰቦች ወይም በቡድኖች ላይ እድሜ፣ መደብ፣ ዘር ወይም ብሄር፣ የፍልሰት ሁኔታ፣ ሃይማኖት፣ የአካል ጉዳተኛነት፣ የፆታ ማንነት እና አገላለፅ፣ ፆታዊ ዝንባሌ ወይም የዘማችነት ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የሚደርስ ጥቃትን የሚያበረታታ ወይም በዋነኛነት ጥላቻን የሚያጋግል/የሚያቀጣጥል ይዘትን የሚያካትት ነው።